# ስለ ሊድ ጥንቃቄ ያድርጉ!

## ሊድ የት ተደብቆ ሊሆን እንደሚችል ያውቃሉ?





**ሊድ ብረት ሲሆን** ልጆችን እና አዋቂዎችን ሊጎዳ ይችላል። ልጆች ላይታመሙ ወይም የታመሙ ላይመስሉ ቢችሉም፣ የደም ምርመራ ግን የሊድ መመረዝ እንዳለባቸው ሊያሳይ ይችላል። ይህም እድገታቸውን፣ ባህሪያቸውን፣ እና የመማር ችሎታቸውን ሊጎዳ ይችላል። በተጨማሪም ሊድ ለአዋቂዎች በተለይም ለነፍሰጡር ሴቶች እና ለልጆቻቸው ችግር ሊሆን ይችላል።



**በቤትዎ ውስጥ ቀለም የተቀባ ሊድ** ሲሰነጣጠቅ ወይም ቅርፊት ሲሰራ፣ የሊድ ቁርጥራጮች ሊወድቁ ወይም የሊድ አቧራ ሊፈጠር ይችላል። ልጆች በወለል ላይ በሚድሁበት ግዜ እነዚህን ቁርጥራጮች ወይም አቧራ ሊያነሱ ወይም እጆቻቸውን እና አሻንጉሊቶቻቸውን ወደ አፋቸው ሊያደርጉ ይችላሉ። በዚህ መንገድ ልጆች የሊድ መመረዝ ሊያጋጥማቸው ይችላል።

**የተወሰኑ መድሃኒቶች፣ ቅመሞች፣ ኮስሞቲክስ፣ እና ከሌሎች ሃገሮች የሚመጡ ምግቦች ሊድ ሊይዙ እንደሚችሉ** ያውቃሉ? በነዚህ ምርቶች ውስጥ ያለው ሊድ ህፃናት እንዲታመሙ ያደርጋቸዋል። እስካሁን ያላወቅናቸው ሌሎች ምርቶች ሊኖሩም ይችላሉ። በአካባቢዎት በሚገኝ መደብር ውስጥ ይሸጡ ይሆናል፣ ወይም ጓደኞች ወይም የቤተሰብ አባላት ወደሌላ ቦታ ከተጓዙ በኋላ ሲመለሱ ሊያመጧቸው ይችላሉ።

## ሊድን ሊይዙ የሚችሉ መድሃኒቶች እና ሌሎች ምርቶች:




### ቅመሞች

ከመካከለኛው ምስራቅ፣ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከህንድ፣ እና ከቻይና የሚመጡሊድ ሊይዙ ይችላሉ።



**ኮስሞቲክስ** ሊድ ሊይዙ ይችላሉ። ኮህል (ወይም ሱርማ ወይም ካጃል ተብሎ የሚታወቀው)፣ አንድ ምሳሌ ነው። ዓይንን ለማድመቅ/ለማጉላት ጥቅም ላይ የሚው ነው።



ከተለያዩ የአለማችን ክፍሎች የሚመጡ በርካታ **የከረሜላ** አይነቶች ሊድ ሊይዙ ይችላሉ።




ከመካከለኛው ምስራቅ፣ ከሰሜን አሜሪካ፣ ከህንድ፣ እና ከቻይና የሚመጡ የዕፅዋት እና የአሩዩቬዲክ **መድሃኒቶች** ሊድ ሊይዙ ይችላሉ።

Images courtesy of The New York City Department of Health

## ከዩናትድ ስቴትስ ውጭ የመጡ **ቅባቶችና የቆዳ መድሃኒቶች** ሊድ ሊይዙ ይችላሉ፥




*yisaoguang yaogua*

የፀጉር ቁስሎችን ለማከም የሚያገለግል የቻይና ቅባት ነው።



*Hondan*

በዳይፐር አማካኝነት የሚከሰትን ሽፍታ እና ደረቅ ቆዳን ለማለስለስ እንደ ቅባት ጥቅም ላይ የሚውል ዱቄት ነው።



*Thanaka*

እንደ ፀሐይ መከላከያ እና ቆዳን ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውል ከበርማ ሃገር የሚመጣ ከዛፍ የሚሰራ ቅባቶት ወይም የቆዳ መድሃኒት ነው።

## የሚያብረቀርቅ የሸክላ

ዕቃ እርሳስ ሊኖረው ስለሚችል የምግብ ዝግጅትና አቅርቦት ላይ ለጥቅም መዋል የለበትም።







## ዕጣን እና አንዳንድ የሻማ መቅረዞች

በውስጣቸው ሊድ ሊይዙ ይችላሉ። ሊድ በከሰል፣ "unsi" እና በቤት ውስጥ በሚያነዷቸው ሌሎች ዕጣኖች እና አንዳንድ የሻማ ክሮች ውስጥ ሊኖር ይችላል።





**የብረት ጌጣጌጦች** ወርቅ ወይም ብር የተቀቡን ጨምሮ ሌሎችም ሊድ ሊይዙ ይችላል። ልጆች በምንም አይነት ሁኔታ የብረት ጌጣጌጦችን ወደአፋቸው ማስገባት የለባቸውም።

Images courtesy of The New York City Department of Health

የሚከተሉት ካጋጠሙዎት፣ ዶክተርዎትን፣ የአካባቢዎትን የጤና መምሪያ፣ ወይም የ የስደተኛ የመልሶ ማቋቋም ስራ አስኪያጅን **ያግኙ፥**

- ቤተሰብዎ ከእነዚህ ምርቶች አንዳቸውን ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ምርቶችን ተጠቅመው ከሆነ።
- በእነዚህ ስዕሎች ውስጥ ስላዩት ማንኛውም ነገር ጥያቄ ካለዎት።
- የሆነ ሰው አዲስ መድሃኒት ሰጥቶዎት ከሆነ ወይም አንድ መድሃኒት ወይም ምርት ለልጅዎ ደህንነቱ የተጠበቀ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ ጥያቄ ካለዎት።
- ቤትዎ የተሰነጣጠቀ፣ የተሸራረፈ፣ ወይም ቅርፊት የሰራ ቀለም ካለው።
- ልጅዎ በሊድ ተመርዟል ብለው ወይም ሊድ ለያዙ ምርቶች ተጋልጦ ሊሆን ይችላል ብለው ስጋት ካደረብዎት። ምንም እንኳን ጤነኛ ቢመስልም እያንዳንዱ ልጅ/ህጻን ደሙ መመርመር አለበት።

